# ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

| | |
|---|---|
| ተዛማጅ ምንጮች: | ABA, ACA, CNA-RB, CND, CND-RA, CNE, FFA, KLA-RA |
| ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት: | በት/ቤቶች ድጋፍ እና ደህንነት ክፍል፤ የስትራቴጂያዊ ስራዎች ቢሮ፤ የዲስትሪክት ስራ ዋና ሀላፊ - Office of School Support and Well-being; Office of Strategic Initiatives; Chief of District Operations |

## የትምህርት ተቋም ስያሜ

**I. ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ FFA የመተግበር ሂደቶችን ለመዘርጋት፣ ስለ ትምህርት ቤት ፋሲሊቲዎች/መገልገያዎች ስያሜ

**II. ዳራ**

A. ትምህርት ቤትን ወይም ተቋምን መሰየም ማለት:- የህዝብን ሀብት/ሪሶርስ መጠበቅ ያለባቸው አይነተኛ አርአያነት ያላቸው፣ ዋና እሴቶች፣ እና የቦርድ ፖሊሲ ACA ጨምሮ በቦርድ ፖሊሲዎች ላይ እንደተገለፀው ሙሉ በሙሉ ለሥራቸው ታማኝ በመሆን ጊዜአቸውን እና ጉልበታቸውን እውቀታቸውን ለማህበረሰቡ ያበረከቱትን በትክክል ለማስታወስ፣ አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት እና የባህል ብቃት፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ብዝሃነትና ልዩነትን በፍትሃዊነት መወከል ነው።

B. በቦርዱ ባለቤትነት የተያዙ ት/ቤቶችን እና የሥራ ማስኬጃ ተቋማትን ኦፊሴላዊ ስሞችን መሰየም የቦርዱ ኃላፊነት ነው። ቦርዱ በፖሊሲ FFA መሠረት ተቀባይነት ያላቸውን ስያሜዎች እና የቦርድ አሠራር ሂደቶችን የትምህርት ቤት መገልገያዎችን መሰየም የትምህርት ቤቶችን ስም መሰየም እና እንደገና የመሰየም መስፈርት አውጥቷል።

C. በአንድ ትምህርት ቤት ወይም ፋሲሊቲ ውስጥ በቦርድ ፖሊሲ FFA መሠረት የማህበረሰብን አስተያየት እና ምክክር በጥንቃቄ ከመረመረ በኋላ፣ በከፊል መሰየም የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ/ተወካይ ሃላፊነት ነው፣ የትምህርት ቤት መገልገያዎችን መሰየም፥ ፖሊሲ ABA፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ; እና ፖሊሲ ACA፣ መድልዎ የሌለበት፣ እኩልነት እና የባህል ብቃት።

**III. የአሠራር ሂደት**

A. አዳዲስ ወይም ድጋሚ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችን መሰየም

1. አዲሱ ትምህርት ቤት እንዲያገለግል የታሰበው የማህበረሰቡ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ፖሊሲ ABA፣ስለ ማህበረሰብ ተሳትፎ የተቀመጡትን ሂደቶች በመጠቀም ምክረሃሳብ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ።

2. የት/ቤት ማህበረሰብ አባላት የተሳትፎ ተግባራት አላማ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን የስያሜ ዝርዝር መፍጠር ሲሆን ቦርዱ የመጨረሻውን ምርጫ ያደርጋል።

   a) ቦርዱ የት/ቤቱ ማህበረሰብ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ እስከ አራት የሚደርሱ ስሞችን

ይሰጣል።

b) በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የተሳትፎ ሂደት እስከ ሁለት ተጨማሪ ስሞች ሊቀርብ ይችላል።

c) ከእነዚህ አማራጮች ውስጥ፣ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ከአራት ያላነሱ ስሞችን የያዘ ቅድሚያ የተሰጠውን ዝርዝር ለቦርዱ መመለስ አለበት።

3. የአዲስ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር ሲሾም እና በተለይም አዲስ ትምህርት ቤት ለመክፈት ከታቀደው ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሚከተለው ይከናወናል:-

a) የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት (OSSWB) ዋና ኃላፊ የሚከተሉትን ያደርጋል–

(1) በማህበረሰብ ተሳትፎ የት/ቤት ስም መምረጥ እንደሚጀምር ለቦርዱ ዋና ስራ አስፈፃሚ ማሳወቅ እና ቦርዱ ከያዘው የትምህርት ቤት ስም ዝርዝር ውስጥ እስከ አራት የሚደርሱ ስሞችን እንዲለይ ይጠይቃል/ትጠይቃለች።

(2) ከርዕሰ መምህር እና ከ OSSWB የአካባቢ ዳይሬክተር ጋር በመነጋገር የ OSSWB አስተዳዳሪ ለማህበረሰብ ተሳትፎ የት/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴን በተባባሪ ሊቀመንበርነት በመምራት እንዲመርጥ ማድረግ (ርእሰ መምህሩ እንደ ተባባሪ ሊቀመንበር ሆኖ ሊያገለግል ይችላል)፤

b) የስትራቴጂክ እንሺኤቲቭ ፅህፈት ቤት (OSI) ኃላፊ ከነባር/ሲንየር የማህበረሰብ አማካሪ ጋር በመተባበር የፍትሃዊነት ተነሳሽነት ዩኒት "Equity Initiatives Unit (EIU)" ወይም EIU ያሰለጠነው ሌላ የማህበረሰብ ተሳትፎ አስተባባሪ የትምህርት ቤቱን አስተባባሪ ኮሚቴ ለመሰየም ይተባበራል የማህበረሰብ ተሳትፎ።

c) ቦርዱ ከያዘው የትምህርት ቤት ስሞች ዝርዝር ውስጥ እስከ አራት የሚደርሱ ስሞችን ዝርዝር ያቀርባል፥ እያንዳንዱ ስም የተጠቆመበትን ምክንያት አጭር ማብራሪያ ይሰጣል።

4. ከ OSSWB/OSI የተመደቡት ተባባሪ ሊቀመንበሮች ለ-- ኃላፊነት አለባቸው:-

a) ት/ቤቱ አገልግሎት እንዲሰጥ የታለመላቸውን ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን እና ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ያቀፈ አስተባባሪ ኮሚቴ በማሰባሰብ ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ተሳትፎ አላማና ተግባራት ማቀድ እና ማከናወን።

b) ስለክንውኖቹ የጊዜ ሰሌዳ፣ ዓላማ እና የተሳትፎ ዓይነት ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ማሳወቅ፤

c) ለቦርዱ እና ለህብረተሰቡ የማህበረሰቡ ተሳትፎ ሂደት ሲጠናቀቅ ማጠቃለያ ሪፖርት ማዘጋጀት –

(1) የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ምክረ ኃሳቦች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች፣

(2) በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የሚቀርበው ማንኛውም ስም(ዎች) በፖሊሲ FFA ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው ስሞችን መስፈርት የሚያሟሉ እና ለትምህርት ቤቱ ትምህርታዊ ተልእኮ እና እሴቶች የሚያገለግል መሆኑን የሚያሳይ ትንታኔ፤ እና

(3) ስለተካሄዱት የህዝብ ተሳትፎ ተግባራት ማጠቃለያ እና የተሳታፊዎች መግለጫ፣ እና

d) ስለ ማጠቃለያው ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ማሳወቅ እና በቀጣይ የቦርድ ውይይቶች ላይ ወቅታዊ መረጃዎችን መስጠት።

5. ስለ ማህበረሰብ ተሳትፎ ማጠቃለያ የቦርድ አፈጻፀም የፖሊሲ FFA ሂደቶችን ይከተላል።

B. ትምህርት ቤትን እንደገና መሰየም

1. ቦርዱ ከተማሪዎች፣ከወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ወይም ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ የተቀበለውን የትምህርት ቤት ስም የመቀየር አቤቱታዎችን ይመለከታል።

a) አቤቱታ በመቀበል ብቻ ቦርዱ የትምህርት ቤትን ስም ለመቀየር ድምጽ አይሰጥም።

b) ቦርዱ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ድጋፍ ያሳየበትን ደረጃ እና በፖሊሲ FFA የተቀመጡትን መስፈርቶች በማሟላት ረገድ የአቤቱታውን ጥንካሬ ይገመግማል።

c) ትምህርት ቤቱ በግለሰብ ስም የተሰየመ ከሆነ፣የግለሰቡን/ቧን ማህበራዊ እና የግል ህይወት በተመለከተ የግል ህይወት ታሪክ ላይ ገለልተኛ ትንታኔ ሊያካሂድ ይችላል።

2. ቦርዱ አቤቱታ አቅራቢዎቹ የሚያስፈልጉትን ነገሮች እንዳቀረቡ ካረጋገጠ፣ ተጨማሪ ውይይቶችን ለማካሄድ የማህበረሰብ ተሳትፎን ሊጠይቅ ይችላል። እዚህ ደረጃ ላይ የሚደረገው የማህበረሰብ ተሳትፎ አላማ አዲስ ስሞችን ለመለየት አይደለም።

3. ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የሚከተለው ይከናወናል፡-

a) የት/ቤቶች ድጋፍ እና ደህንነት (OSSWB) ሃላፊ ከርዕሰ መምህር እና OSSWB የአካባቢ ዳይሬክተር ጋር በመመካከር ለማህበረሰብ ተሳትፎ የት/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴን በረዳት ሊቀመንበርነት የሚያስተባብር OSSWB አስተዳዳሪ በመለየት ኃላፊነት ይሰጣል። ርእሰ መምህሩ እንደ ምክትል ሰብሳቢ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

b) የስትራቴጂክ ተነሳሽነት ፅህፈት ቤት ሃላፊ (OSI) ሲንየር/የበላይ የማህበረሰብ አማካሪ ጋር ከፍትሃዊነት ተነሳሽነት ክፍል (EIU) ወይም EIU ያሰለጠነው ሌላ ግለሰብ የት/ቤቱን የማህበረሰብ ተሳትፎ ኮሚቴ እንዲመራ የማህበረሰብ ተሳትፎ አስተባባሪ ይመድባል።

4. የ OSSWB እና OSI ተባባሪ ሰብሳቢዎች የሚከተሉትን ያከናውናሉ –

a) የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ተወካይ የሆኑ ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን እና ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ያቀፈ አስተባባሪ ኮሚቴ የማሰባሰብ አላማው የማህበረሰብ ተሳትፎ ተግባራትን ለማቀድ እና ለማከናወን ነው።

b) ለተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ሰራተኞች እና የት/ቤቱ ማህበረሰብ ተማሪዎች ቦርዱ የት/ቤቱን ስም ለመቀየር አቤቱታ እንደደረሰው እና የሚከናወኑትን ነገሮች የጊዜ ሰሌዳ፣ አላማ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን ማሳወቅ፣

5. የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የቀድሞ ተማሪዎች በፖሊሲ ABA፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ ላይ የተዘረዘሩትን የማህበረሰብ ተሳትፎ ሂደቶችን በመጠቀም ምክረሃሳብ ይሰጣሉ–

    a) ለአሁኑ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ስያሜው የሚሰጠው ትርጉም፣

    b) በግለሰቦች ስም ለተሰየሙ ትምህርት ቤቶች፣ የግለሰቡ ሕይወት የትምህርት ቤቱን ትምህርታዊ ተልዕኮ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ እሴቶች፣ የቦርድ ዋና እሴቶችን እና/ወይም ፖሊሲ ACA የሚረጋገጥበት ደረጃ፣ እና

    c) በአቤቱታው ላይ የተገለጹትን ስጋቶች ለመፍታት ያሉትን አማራጮች።

6. በማህበረሰቡ የተሳትፎ ተግባራት ማጠቃለያ ላይ፣ ተባባሪ ሊቀመንበሮች ለማህበረሰቡ እና ለቦርዱ ማጠቃለያ ሪፖርት የማዘጋጀት ሃላፊነት አለባቸው –

    a) ለአሁኑ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ስያሜው የሚሰጠውን ትርጉም እና በማህበረሰቡ ተሳትፎ ሂደት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ጥያቄዎችን ለመፍታት የት/ቤት ማህበረሰብ አስተያየት ትንተና፣

    b) በግለሰቦች ስም ለተሰየሙ ትምህርት ቤቶች፣ የግለሰቡ ሕይወት የትምህርት ቤቱን ትምህርታዊ ተልዕኮ በማሳካት ረገድ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ እሴቶች፣ የቦርድ ዋና እሴቶች እና/ወይም ፖሊሲ ACA የሚያረጋግጥበትን ደረጃ ማጤን፣

    c) ስያሜው እንደገና ሲቀየር በትምህርት ሥርአቱ የሚያስከትለውን ወጪ ተነፃፃሪ ትንተና፣

    d) የተከናወኑ የማህበረሰብ ተሳትፎ ተግባራት ማጠቃለያ ሪፖርት እና የተሳታፊዎች መግለጫ፣ እና

    e) ስለ ማጠቃለያው ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ማሳወቅ እና ስለቀጣዮቹ የቦርድ ውይይቶች ወቅታዊ መረጃዎችን መስጠት።

7. የማህበረሰብ ተሳትፎ ማጠቃለያው የቦርድ አሠራር ፖሊሲ FFA ላይ የተደነገገውን ይከተላል።

C. በከፊል የትምህርት ቤት መገልገያዎች

1. የ OSSWB ኃላፊ፣ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተወካይ እንደመሆኑ(ኗ)፣ በከፊል የትምህርት ቤትን ፋሲሊቲ ለመሰየም በወቅቱ ካሉት ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች የቀረበውን አቤቱታ ማጽደቅ ይችላል/ትችላለች።

2. አመልካች(ቾች) ሀሳቡን ለት/ቤቱ ርእሰ መምህር ማቅረብ አለባቸው፣ እና በአቤቱታው የተጠየቀውን የትምህርት ቤቱን ፋሲሊቲ ስያሜ እና የተጠየቀውን ስም ለመገምገም በሚከተለው ሁኔታ በቂ መረጃ ማካተት አለበት።

    a) እቃ

(1) የትምህርት ቤትን መገልገያ በከፊል ስያሜ ስለመስጠት ወይም እንደገና እንዲሰየም የፋሲሊቲ ማሻሻያ የሚያስፈልገው ማንኛውም ጥያቄ ፖሊሲ CNE ጨምሮ፣የሚመለከተውን የቦርድ መመሪያዎች እና የMCPS ደንቦችን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ባጀት/ወጪ ያልተመደበለት የተቋማት ማሻሻያዎች ድንጋጌዎችን ማክበር አለበት።

(2) አቤቱታው ጠንካራ የወጪ ትንተና ማቅረብ እና በቂ ገንዘብ ወይም የገንዘብ ማሰባሰብያ ፕሮፖዛል ከደንብ CNA-RA፣ ገንዘብ ማሰባሰብ እና ደንብ CNA-RB፣ ማስታወቂያ ጋር ያገናዘበ መሆን አለበት።

b) ስም

ደንብ CNA-RB፣ ማስታወቂያ፣ መዋቅራዊ ቅርጾች ላይ የመታሰቢያ መልእክቶችን ይፈቅዳል፣ እና በፖሊሲ FFA መሠረት ከሚከተሉት የተለዩ ሁኔታዎች በስተቀር ትምህርት ቤቶችን የመሰየም መመዘኛዎች በት/ቤት መገልገያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

(1) በከፊል የትምህርት ቤት መገልገያ በግለሰብ ስም የሚጠራ ከሆነ፣ ለትምህርት ቤቱ፣ ለማኅበረሰቡ፣ ለካውንቲው፣ ለስቴቱ ወይም ለመላው ህዝብ የላቀ አስተዋጽዖ ላደረጉ በህይወት ለሌሉ (የግዴታ ባይሆንም) የት/ቤት መገልገያዎች በከፊል በስማቸው እንዲሰየም ይመረጣል።ግለሰቡ(ቧ) በአሁኑ ጊዜ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቀጣሪ ካልሆነ(ች)፣ በሥራ ላይ ካልሆኑ፣ ወይም በአሁኑ ጊዜ የህዝብ ተመራጭ ካልሆኑ/ወይም ለመመረጥ ፍላጎት ከሌላቸው በህይወት ያለ ሰው ስም በከፊል የትምህርት ቤት ተቋም/መገልገያ በስማቸው ሊሰየምላቸው ይችላል።

(2) በህይወት የሌሉ ተማሪዎችን ለማስታወስ የትምህርት ቤት መገልገያዎችን በከፊል በስማቸው ለመሰየም የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም። በአንዳንድ ሁኔታዎች የቀረበውን ሀሳብ የተቃውሞ ሃሳብ ለማቅረብ፣ ርእሰ መምህሩ(ሯ) ከስነልቦና አገልግሎት ዲሬክተር ጋር መማከር አለበ(ባ)ት።

3. ርእሰ መምህሩ(ሯ) አቤቱታው እንደደረሰው/እንደደረሳት ማሳወቅ አለበ(ባ)ት።

a) ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ አቤቱታውን ገምግመው ማናቸውም ያልተሟሉ ነገሮች ካሉ ለአመልካቾቹ ማሳወቅ አለባቸው። አመልካች(ቾች) በተገቢው ሁኔታ አቤቱታውን ገምግመው እንደገና ማቅረብ ይችላሉ። ቀጣይ እርምጃዎች ከመወሰዳቸው በፊት አቤቱታው የተሟላ መሆን አለበት።

b) የተሟላ አቤቱታ መድረሱን ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ ለአመልካቹ(ቾች) እና ለ OSSWB/ለተወካይ ያሳውቃል።

4. ርእሰመምህሩ(ሯ) በፖሊሲ ABA ላይ በተገለጸው መሰረት ማህበረሰቡን በማሳተፍ ረገድ ርእሰመምህሩን/ተወካይን ለመርዳት EIU የሰለጠነ የማህበረሰብ ተሳትፎ አስተባባሪ ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል።

5. ርእሰ መምህሩ/ተወካይ የሚከተለው ኃላፊነት አለባቸው–

a) የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚወክሉ ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን እና

ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ያቀፈ አስተባባሪ ኮሚቴ መሰብሰብ፤

b) በክፊል የትምህርት ቤቱን መገልገያ የሆነ ስያሜ ለመስጠት የቀረበውን ጥያቄ እና የጊዜ ሰሌዳውን፣ ዓላማውን እና የማህበረሰቡን የተሳትፎ ተግባራት የሚያካትት አቤቱታ እንደደረሰው/እንደደረሳት ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና የማህበረሰቡ አባላት ለሆኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች ማሳወቅ–

(1) ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ለአስተባባሪ ኮሚቴው የህዝብ አስተያየት እንዲሰጡ ከ21 ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት፣ እና

(2) አቤቱታውን እና የህዝብ አስተያየቶችን ለመገምገም እና ለመተንተን ከአስተባባሪ ኮሚቴው ጋር ምክክር ማድረግ እና ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ለተወካይ አስተያየት መስጠት፣ እና

c) ለማኅበረሰቡ እና ለ OSSWB ኃላፊ፣ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተወካይ ለመሳሰሉት የማህበረሰቡን አስተያየት እና የአስተባባሪ ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ የሚያጠቃልል መግለጫ ማዘጋጀት።

6. አስተባባሪ ኮሚቴው የOSSWB ኃላፊ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ እንዲያደርግ፣ እንዲያጸድቅ ወይም፣ ከጠያቂዎቹ ጋር በመነጋገር የውሳኔ ሃሳቡን ማሻሻያ እንዲያደርግ ምክረሃሳብ መስጠት ይችላል።

a) ርእሰ መምህሩ እና EIU ያሰለጠነው/ያሰለጠናት ጉዳዩን የሚያስተባብር ሰው፣ ድምጽ የማይሰጡ የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ናቸው።

b) ርእሰ መምህሩ የአስተባባሪ ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ ለጠያቂው አካል እና ለሚመለከተው OSSWB የአካባቢ ዳይሬክተር ያሳውቃል።

7. አግባብ ያለው OSSWB የአካባቢ ዳይሬክተር የተቀበለውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ ይመረምራል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ፋሲሊቲዎችን ከሚያስተዳድረው ዳይሬክተር ጋር ይመክራል፣ እና OSSWB ኃላፊ የቀረበውን ምክረሃሳብ ውድቅ እንዲያደርግ ወይም እንዲስማማ ይመክራል። OSSWB ኃላፊ/ተወካይ ውሳኔያቸውን ለርእሰመምህሩ እና ለአመልካች(ቾች) ያሳውቃሉ፤ እንዲሁም MCPS ደንብ KLA-RA መሰረት አመልካች(ቾች) ይግባኝ የማለት መብት እንዳላቸው ይገልጹላቸዋል፣ ከህዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት።

D. የቡድን ተምሳሌታዊ አርማ/Mascots

ፖሊሲ ACA፣ አድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት፣ ቦርዱ አርማዎችን፣ መለያ ምልክቶችን/ሎጎ፣ የቡድን ስሞችን፣ ዜማዎችን፣እና የሙዚቃ እጀባዎችን የሚያበረታታ ሲሆን፣ አካታች የሆነ፣ ከአድሎ የጸዳ፣ እንዲሆን እና ለሁሉም ሰው ተስማሚ/ምቹ እንዲሆን ያበረታታል። OSSWB ኃላፊ፣የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ –

1. በትምህርት ቤት ደረጃ ምክክር በማድረግ እና የት/ቤት ማህበረሰብ ግብአቶችን በጥንቃቄ ከመረመረ በኋላ የት/ ቤቶች የቡድን ተምሳሌታዊ አርማ ወካይ ምስልን ያፀድቃል፣ እና

2. ከላይ ክፍል IV.C.4 ላይ ከተቀመጡት ሂደቶች ጋር የሚጣጣም የማህበረሰብ ግብአት

መመሪያዎችን ሊያዘጋጅ ይችላል።

**ስለ ደንቡ ታሪክ፡-** የበፊት ደንብ ቁ. 230-5፣ አክቶበር 1982 ተሻሽሏል፣ኖቬምበር 26 ቀን 1997 ተሻሽሏል፣ ጁን 29, 2000 ተሻሽሏል፤ ኤፐሪል 25, 2005 ተሻሽሏል፣ ኖቬምበር 17 ቀን 2005 ተሻሽሏል፣ ኖቬምበር 28 ቀን 2006 ተሻሽሏል፣ አክቶበር 14 ቀን 2010 ዓ.ም ተሻሽሏል፣ ኦገስት 7, 2014 ተሻሽሏል፣ ጃኑዋሪ 3, 2018 ተሻሽሏል፣ አክቶበር 31, 2022 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

<table>
<tr><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org